# ግልፅ ደብዳቤ

ለኢንጅነር ኃይሉ ሻውል
ለሰሜን አሜሪካው የላእላይ ምክር ቤት ልኡክ አባላት
ሰሜን አሜሪካ

ሴትዮዋ ባለቤቷ በሄደበት ቦታና ላገኛቸው ሰዎች ሁሉ እየዋሸ በጣም ያስቸግራታል።እሱ በዋሸ ቁጥር እሷ መግቢያ ታጣለች።እንዲያው ከመሬት ተነስቶ መተርተርነው።መዋሸት ነው። መቅደድ ነው።በዘመኑ ስጥ የሚሉት አይነት ነው።

አንድ ቀን ቤተሰቦቿ ወዳሉበት ቦታ ስለተጋበዙ መሄድ ግድ ሆነ ስለዚህም ሚስት እንዲያው ረጋ ብላ ቀስ ብላ አግባብታ እባክህ እንዲያው አንተ ስትቀልድ ሌላው እውነት እየመሰለው ዋሸ ይሉሃል ያ ደሞ እኔን ያሳፍረኛልና እባክህ አትዋሽ ትለዋለች። በዘዴ። ስትቀልድ ያለችው ስትዋሽ ብትለው ውሸታም አልሽኝ የሌለብኝን ብሎ ሊዋሻት ነውና።ወጣም ወረደ እሱ ላይዋሽ ቃል ገብቶላት እንዲያው ድንገት ተሳስቼ ብዋሽ ቀስ ብለሽ ረገጥ አድሪጊኝ ይላታል። በዚሁ ይስማሙና ወደ ተጠሩበት ይሄዳሉ። በጨዋታ መሃል አርፎ የተቀመጠው ባል በል በል ይለውና « ትላንት በሰፈራችን እባብ መጥቶ ይገርማችኋል ቁመቱ 8 ሜትር ይሆናል» ሲል ሚስት በተስማሙበት መልክ ቀስ ብላ እግሩን ረገጥ ስታደርገው «ቁመቱ ከስድስት ኪሎ ሃውልት ይበልጣል» ሲል እንደገና ስትረግጠው ደሞ ምን አለፋችሁ በቁመቱ ቢጋደም እኮ ጃንሜዳን ከጫፍ እስከጫፍ ያዳርሳታል» ብሎት አረፈው።

ባለፈው ማክሰኞም የዚህ ተመሳሳይ ነው የሰማሁት።
የአሜሪካን ሬዲዮ ጣቢያ ኢንጅነር ሃይሉ ሻውልን ያነጋግራል።በመጀመርያ ኢንጅነር ስለስብሰባውና ስለነበሩት አባላት እንዴት ሆነ የሚለውን ፍርጥ አድርገው ሊናገሩ አልፈለጉም አለያም አልቻሉም።በመጀመርያ ለላእላይ ኮሚቴው የቀረበው የጉዞ ፕሮግራም ሲጠነሰስ ውይይት የተካሄደበትና ቤቱም የተቀበለው «ከሃገር ውጪ ያሉት ደጋፊዎቻችን በጣም የሚያኮራና የሚያስመካ ሥራ ሰርተዋል በተለይ እኛን ለማስፈታትና ትግሉም በሰላማዊ መንገድ እንዲቀጥል፣ ኤች አር 2003 ም እንዲያልፍ የከፈሉት መስዋእትነት ከባድ በመሆኑና በኛ መታሰር የተነሳ የተፈጠረውን ክፍተት ለመሙላት በተወሰደው እርምጃ አለመግባባት በመፈጠሩ ሄደን ማስረዳት ማስማማት መንገድ ማስያዝ አለብን በሃገር ውስጥ መቼም በተገባልን የሽምግልና ቃል መሰረተ አንዳችም የተከወነ ጉዳይ ካለመኖሩም በግልጽ ሕዝቡን ጠርተን ለማወያየት ፈቃድ የለንምና ብናደርገው ለአደጋ እናጋልጠዋለን» የሚለውን ነው።

ለነገሩ ኢንጅነር በወቅቱ ታመው በስብሰባዎች ላይ ባይገኙም በአግባቡ በየእለቱ የሚደረገውን ውይይትና የተደረሰበትን ውሳኔ የሥራ አስፈጻሚ አባላት በቤትዎ እየተገኙ በግምባር በማስረዳት እንዲያውቁት አድርገዋል።ተቃውሞ ሲኖርዎትም በአብላጫ ድምጽ ያለፈውን መቀበል የዴሞክራሲ ባህልና የቅንጅትም መመርያና እምነትም ነውና ተቀብለዋል።ገና ውይይቱ ያላለቀለትም ከሆነ ሃሳብዎን ሰጥተው ለቤቱ እየቀረበ ተስተናግዷል።እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ ላእላይ ምክር ቤቱ ባለው ጨዋነትና ከበሬታ የተወሰነን ጉዳይም ከእርስዎ በተነሳ ቅሬታ እንደገና እንየው ተብሎ የታየበትም ጊዜ እንደነበረ ግልጽ ነው።

እስቲ አንድ ጥያቄ ላንሳ። ለመሆኑ ኢንጅነር በምር ያን ሁሉ ስብሰባ ያልተገኙበት በህመም ምክንያት ነው? ዛሬ እመጣለሁ ጠብቁኝ ብለውስ የምክር ቤት አባላት ሲጠብቁ የመምጫዎ ሰአት አልፎ ከአንድ ሰአት በላይ አርፍደው በመጨረሻው በስልክ አልቻልኩም ያሉት ስንት ጊዜ ነው።

ኢንጅነር ቅንጅት የሚያምነው «ከድርጅት ፍቅር የሃገር ፍቅር ከራስ ጥቅም የሕዝብ ጥቅም ይቅደም» በሚለው ነው፡፡ቆይ እርስዎ እኔ ነኝ መወሰን የምችለው ማለትዎ በእርስዎ አባባል መሰረትም ብንሄድ ከተገኙት 19 የላእላይ ምክር ቤት ስብሰባውን የተከታተሉና ውይይት አድርገው ሃሳብ አቅርበው ከነበሩት ይበልጥ እኔ እበልጣለሁ ነው?የቅንጅት ደንብና መመርያ የሚለው አንድ ሰው አንድ ድምጽ ሆኖ እያለ በየትኛው ስውር ደንብ ነው እርስዎ የሚበልጡት? ይሄ እኮ የቁመት ወይም የአገልግሎት ዘመን ብልጫ አይደለም የሕግ ጉዳይ የዴሞክራሲ ስርአት ነው፡፡ስለዚህም እኔም እርስዎም ያም ይሄም ያለን የድምጽ ዋጋ እኩል ነው፡፡የአለቃ ድምጽ የሚበልጥበት ቦታ ወያኔ/ኢህአዴግ አምባ ነው እኛ ደሞ ቅንጅት ነን፡፡

ለመሆኑ ስንት የላእላይ ምክር ቤት አባላት ናቸው አሁን በከተማው ያሉት? ከእነሱስ መሃል ከታሰሩት ውጪ ለዚህ ስብሰባ ማንም መቀላቀል የለበትምስ ያሉት እርስዎ አልነበሩም? ላስታውስዎት ከነቃልዎ፣ .......**«ወደ ፓርላማ የገቡትም ሆኑ ሳይገቡ ሽምቀው የቆዩት አቋማቸው እንዲህ ነው ለማለት ስለሚያስቸግር የያዝነውን አጀንዳ ጨርሰን በኋላ እንዴት ከኛ ጋር ይቀላቀሉ የሚለውን እንወስናለን»** ብለው ነበር እኮ ረስተውት ነው?

ለመሆኑ ሻለቃ አድማሴና ዶ/ር በዛብህ ቅንጅትን ወክለው እንዲሄዱ ሲወስኑ እርስዎ ከማንም ጋር ሆነው ነው?፣ሌላው ቢቀር በአንድ ዞን አብሮዎት ከነበሩት ጋር አለመነጋገርዎና ከበድሩ አደም ጋር መወሰንዎ ምልአተ ጉባኤ ሆናችሁ ነው? ረስተውት ካልሆነ ተዉ ሲባሉም አሻፈረኝ ነው ያሉት፡፡

ወደ ስብሰባው አልተጋበዝኩም ያሉትስ? እንዴ ምን ነካዎት ኢንጅነር? ስንት ጊዜ ጥሪ ሲደረግልዎ እየሰማን? በአዲስ አበባስ እያሉ እኔ ወደ ጀርመን እንጂ ወደ አሜሪካ አልሄድም ካሉ በኋላ ላእላይ ኮሚቴው አባላት እንዲያነጋግሩዎት ልኮ አልቀበልም አላሉም፡፡የላእላይ ምክር ቤቱን ውሳኔ አሻፈረኝ ያሉት ስንት ጊዜ ነው?

እርስ በርስ ጓደኛሞች ተመራርጠው የሚሉትስ ረሱት እንዴ እርስዎ ነዎት እኮ እያንዳንዱንም አባል የመደቡትና የተመደበውንም ያጸደቁት፡፡

ደሞስ ማና ማንን ነው ጓደኛሞች የሚሉት? አባይነህ ብርሃኑን? ጌታቸው መንግሥቴን?ማንን ከማን ሊያጣምዱ ነው? በውነት በጣም ነው ያዘንኩት፡፡እርስዎስ ላእላይ ምክር ቤቱ ከወሰነው ውጪ ወደ ተጎዱ ሰዎች ቤት ለመሄድ ማን ውክልና ሰጠዎት? ማንስ በድሩን ወከለልዎት? ለመሆኑ ለምን ነበር ላእላይ ኮሚቴው መጠየቁ ይቆይ ያለው? ይህንን ሳያውቁ ቀርተው ሳይሆን ይቺን በማድረግ በጋዜጣ ላይ ወሬው እንዲወጣና ርካሽ ተወዳጅነት ለማግኘት በእቅድና በፕላን የተያዘን ጉዳይ መሃል ገብታችሁ መነገጃ ነው ያደረጋችሁት?፡፡ይህስ የላእላይ ምክር ቤቱን ውሳኔ መጣስ አይደለም?እንደገና ላስታውስዎ የተጎዱትን ቤተሰቦችም ጉዳይ ቢሆን ባንድ ቀን ድጎማ ሳይሆን ለዘላቂው ከደጋፊዎቻችን ጋር በመመካከር ዘላቂ ገቢ የሚፈጠርበትን በማመቻቸት እንሰራለን ተብሎ ተወስኖ እርስዎስ አምነውበት ይሁንታ ሰጥተውት አልነበረም?

ኢንጅነር

ያገራችን ተረት በሬ ካራጁ ይውላል ነው፡፡እርስዎም በውነትና ከአንጀት ከእርስዎ ጋር የቆሙትንና ለለበጣና ለጊዜያዊ ጥቅም አብሮዎት የቆሙትን መለየት አልቻሉም፡፡አንዳንዶቹ የመዋእለ ነዋይ ችግር ያለባቸው፣ሌሎቹ የመታመን ጣጣ የከበባቸው፣ በሌላ በኩል ከምንም በላይ ለግል ዝናና ጥቅም የቆሙ፣የሂሳብ ምርመራን ሃቅ የሚሸሹ፣ የነበሩበትን ሃላፊነት በአግባቡ ለባለመብቱ ሳያስረክቡ ተሽፋፍነው የጠፋ ስምን ለማደስ መንገድ የሚመርጡ፣እነዚህ ናቸው ዙርያዎን የከበቡዎት፡፡በጥላቻ ወይም ሳያመልከኝ አለያም ስገባ ስወጣ ቁጭ ብድግ አላለም በሚል የቆሙለትን ዓላማ ገደል አይክተቱት፡፡

ትዝ ይልዎት እንደሆን የተወሰንን ሰዎችን በቤትዎ እየጠሩ ስብሰባ ሲደረግ ያውም የቀድሞ የመኢአድ አመራር አባላትንና አያስፈልጉም የተባሉ ተመራጭ አመራር አባላትን በአዳዲስ በተኩበት ጊዜ

ለብቻ አግኝቼዎት ይህ አካሄድ የቆምንለትንና የታሰርንለትን የቅንጅትን እምነት የሚሸረሽር ነው ብዬዎት ነበር።

ይህ ሁኔታ ለጠላት በር ይከፍታልና ለምን ቢሯችንን ዘግተን ልዩነታችንን አናጠራም? ብዬዎት ነበር

ሕዝቡንም ሃገርንም ለከፋ ተስፋ መቁረጥ ለባሰ መከራ ያጋልጣል ብዬዎት ነበር

ኢንጅነር

በጣም ነው የማዝነው።ተሳስተዋል።ቃልዎን አጥፈዋል።ለሃገርና ለሕዝብ ሲባል የተከፈተ በርን ዘግተው ወደ ጨለማ እየሄዱ ነው

በላእላይ ምክር ቤቱ ተወክለው ሊያነጋግሩዎ የመጡትን ዶ/ር ኃይሉ አርአያንና አቶ ክፍሌ ጥግነህን ምን ብለው ነው የመለሷቸው? ምንስ መልእክት ነው ለላእላይ ምክር ቤቱ ያስተላለፉት? ይህን ሁሉ የቻለ ላእላይ ምክር ቤት ነው አሁን የሚወገዝና የሚወቀሰው? እርስዎ የሚሉት እውነት የሁሉም ሰበብ ህክምናዎ ከሆነስ፣ለምን አልሄድም ከናንተ ጋር አልቀላቀልም የምሄደውም ወደ ጀርመን ነው ካሉና ካስታወቁ በኋላ «ቡድኑ በላእላይ ምክር ቤቱ ውሳኔ መሰረት ተንቀሳቀስ ሄደ» ሲባልና አቀባበሉ የገነነ የሞቀ መሆኑ ሲታወቅ ለምን ሃሳብዎንና በጀርመን የማይታጠፍ የማይለወጥ የሃኪም ቀጠሮ አለኝ ያሉትን ለወጡ?

ኢንጅነር

አልሰሙም እንዴ  በእርስዎ ቤት በነበረው ስብሰባ ላይ ግንባር ቀደም ከነበሩት አቶ አባይነህ ብርሃኑ በአውሮፓው ልኡክ ውስጥ ሆነው  ሻለቃ ጌታቸው መንግሥቴ በደቡብ አፍሪካው ቡድን ውስጥ ሆነው ላእላይ ምክር ቤቱ የሰጣቸውን ሃላፊነት በመወጣትና አንዳችም ቅሬታ ያላሳዩ መሆናቸውን?ማሙሸት አማረም ወደ ካናዳ ለመሄድ ቪዛውን እየጠበቀ መሆኑን አላወቁም?

በቃለ መጠይቅዎ ላይ እንዳሉት አዎን አሁን ቅንጅት ቢሮዎቹ ስለተዘጉ በቀድሞው መኢአድ ቢሮ ውስጥ ነው አንዳንድ ሥራዎችን የሚያካሂደው። እውነቱ ግን የቅንጅት ሥራ ነው ወይ የሚካሄደው? ላእላይ ምክር ቤቱ ጉዞውን ሲወስንና ልኡካኑ እንቅስቃሴ ሲጀምሩ ጊዜያዊ የአስተዳደር ኮሚቴ አዋቅሮ ስላልተፈቱት አባላትና ደጋፊዎች፣ ከሽማግሌዎቹ ጋር ሊደረግ ስለሚገባው ግንኙነት፣ስለቅንጅት ሕጋዊነትና ስለሌሎችም ጉዳዮች ኮሚቴዎች ተዋቅረው እየሰሩ ነው።በቢሮው ውስጥ ግን ያሉት እርስዎ ያስቀመጧቸው ከፋፋዮች የሆነ ያልሆነውን በማውጠንጠንና በማቀባበል ቅንጅትንና አመራሩን፣ላእላይ ምክር ቤት ያሰማራቸውን ልኡካን በማብጠልጠልና የጋዜጣ ማሻሻጫ የሚያደርጉ ናቸው።ያም ሆኖ ወጪው ሁሉ ግን የሚሸፈነው በቅንጅት ገንዘብ ነው።በዚያ ቢሮ ውስጥ ካሉት መሃል በግንባር ቀደም መኢአድን ማጠናከርና መኢአድን መልሰን በቦታው ማስቀመጥ አለብን የሚሉት እንዲህ ተባለ እንዲህ ሆነ በማለት አሉባልታ በመሰብሰብ ላረጀ አስተሳሰብ የሚንቀሳቀሱ ናቸው።የራሳቸውን ቡድን አዋቅረው ስላልተፈቱት አባላት የሚደረገውን እንቅስቃሴ፣ ሕጋዊነትን ለማረጋገጥ የተጀመረውን ሂደት ለማሰናከል የሚንቀሳቀሱ ናቸው።

ኢንጅነር

የተናገሩት ከሚጠፋ የወለዱት ይጥፋ» ይባላል እኮ።ከጅምሩ ገና ሀ ሲባል ሻለቃ አድማሱንና ዶ/ር በዛብህን በግል ስልጣንዎ ከፓርቲ ደንብና መመርያ ውጪ ልኡካን አድርገው ሲልኩ ማንን አማከሩ? ከማን ጋር ወሰኑ?እንዲያውስ አይሆንም ይሄ ጉዳይ በአመራሩና በአባላቱ መሃል ቅሬታ ይፈጥራል ብለው ሲመክሩዎት፣«የኔን ውሳኔ ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ አባል አይኖርም አመራሩም ቢሆን የሊቀመንበሩን ውሳኔ ሊቀበል ይገባል» ሲሉ ትዝ ይልዎት እንደሆነ አንድ ሰው ሳቀ፣ምን እንዳሉት ያስታውሳሉ?አሁን በዚህ ጽሑፍ ላይ አንስቼ የባሰ ግምት ውስጥ እንዲገቡ ስለማልፈልግና እንደተከበሩ እንዲቀጥሉ ስለምፈልግ ሕሊናዬም ተው ስላለኝ አላነሳውም።

ላእላይ ምክር ቤት ስንል ማንን ማለት ነው የሚል ጥያቄ እርስዎ በነበሩበት ስብሰባ ቃሊቲ በፍርድ ቤት ትእዛዝ ለመሰብሰብ በቻልንበት ወቅት ከዶ/ኃይሉ አርአያ ተነስቶ ነበር።የተነሳበት ምክንያት ሳስታውስዎ።«ውሳኔያችንን ውጭ ላለው ደጋፊና ለሚንቀሳቀሰው አካል ማስታወቁን በተመለከተ በቃሊቲ ያለው የላእላይ ምክር ቤት አባል በወሰነው መሰረት ተብሎ ይላክ» ሲሉ ነበር።ወዲያው « ለምን በቃሊቲ ያለው ውጭ ያሉትም አባላት ይህን ጉዳይ ተነጋግረውበት አንድ ይዘት ቢኖረው አይሽልም ወይ?» የሚል ጥያቄም ተነስቶ እርስዎ ሲመልሱ«ውጭ ያሉት ስንል ማንን ከማን ለይተን ነው?አሁን ባለንበት ሁኔታ ማነው ከኛ ጋር ለቅንጅት የቆመ? ማነው ከሌላ ጋር የወገነ? ማን አብሮን ይቀጥላል? ማን በሌለንበት ጊዜ የቅንጅት ሕልውና እንዳይከስም ይታገላል? ማን መሳርያ ሆኖ እየመታን ነው? የሚለውን ለይተን ባላጣራንበት ወቅት በጅምላ ሁሉንም እናካት ማለቱ አደጋ አለው።አንዱ ተነስቶ እኔ በዚህ ጉዳይ የለሁበትም ምንም የማውቀው ጉዳይ የለም ብሎ በጋዜጣ ቢለፍፍ ምን ልናደርግ ነው።? እንደምታውቁት አሁን ቢያንስ ሁለት ቅንጅቶች አሉ አዚህ ደሞ እኛ አለን ሶስት መሆኑ ነው ስለዚህ ከሃገር ውጪ ያለውንም ኮሚቴ ያቋቋምነው በእሥር ላይ ያለነው ስለሆንን ይህንኑ ይዘን መቀጠሉ ከብዙ ነገር ያድነናል» ነበር ያሉት። ታዲያ ቃለ ጉባኤ አልተያዘም ወይም ከታሰርነው ውጭ ማንም አልሰማም ካልሆነም ይህን ጉዳይ በተመለከተ ጋዜጣዊ መግለጫ አልሰጠንምና ሕዝብ አያውቀውም በማለት ነው የትኛው ላእላይ ምክር ቤት የሚሉት?

ከወጣንስ በኋላ ያልታሰሩትን አባላት በተመለከተ አሁኑኑ ይካተቱ ወይስ ቀደም ተብሎ እንደተባለው ከማጣራቱ በኋላ ይካተቱ በሚለው ጉዳይ ላይ ሥራ አስፈጻሚው ተነጋግሮ ያንን እርስዎ በህመም ምክንያት ባለመገኘትዎ በተወካዮች ለርስዎ ሲቀርብ በፊት በተወሰነው መሰረት ይሁን ማን የት እንዳለ ይለይ ብለው አልወሰኑም? ይህን መቼም አይዘነጉትም።

ኢንጅነር

ለመሆኑ እርስዎ እራስዎ በአንደበትዎ ጉዞው እንዲዘገይ፣ሚሌኒዬምን በሃገር ውስጥ እንድናከብር ጠይቂ ነበር ያሉትስ ማንን ነው የጠየቁት?አሁን የትኛው ላእላይ ምክር ቤት የሚሉትን? ነው ወይስ ሳናውቅ ሁላችንንም ሰብስበውን ነበር? ይተዉ ኢንጅነር የሚናገሩት ሁሉ እርስ በርሱ የሚቃረን ነውና ይመከሩ።

በቃለ ምልልሱ ላይ የትኛው ላእላይ ምክር ቤት ሲሉ ተደምጠዋል።ያ እርስዎ መጣሁ እያሉት በጎን ሌላ ስብሰባ ሲያካሂዱበት የነበረው ላእላይ ምክር ቤት ነው።ለነገሩ እንዳሉት ቢሆንስ 19 አባላት ቢሆኑስ የተሰበሰቡትና የወሰኑት የእርስዎ አንድ ብቸኛ ድምጽ ያውም የላእላይ ምክር ቤቱን ስብሰባ ያልተሳተፉትና ከዚያ ውጪ በቤትዎ ከተወሰኑ ሰዎች ጋር ባደረጉት ስብሰባ የተወሰነውን ድብቅ አጀንዳ ነው ይበልጣል የሚሉን?ለመሆኑ ከዚያ የድብቅ ስብሰባ ላይ አቶ ብሩክ ሁለተኛ እንዳይገኝ ብለው ለምን ውሳኔ አሳለፉ? ሃሳብዎን ስለተቃወመ አይደለም? ኢንጅነር ዝም በማለታችን አያውቁም አይበሉን እናውቃለን።እኔንስ ለምን በቀጣይ የርስዎ የቤተመንግሥት ስብሰባ ላይ እንዳልገኝ አደረጉ «የለም አይሆንም ይሄ ነገር ከሕዝብ ያለያየናል፣ለጠላት መሣርያ ያደርገናል ስላልኩ አይደለም።ግን አሁንም በመጨረሻው ቀን ማለት እኔ በተገኘሁበት ቀን የተባባልነውን አይዘንጉ። እርስዎ ይህ አካሄድ እኔን ለማጥፋት ስለሆነ ለማንም ቢሆን ሰላም የሆነ ቅንጅት አላስረክብም ሁሉም እንዳማራው ይቀራል ሲሉኝ ቅንጅት እኮ የሕዝብ እንጂ የማንኛችንም አይደለም ብዬዎት ነበር አሁንም እውነቱን ነው የርስዎም የዶ/ር ብርሃኑም የወ/ሪት ብርቱካንም፣ የአቶ ሙሉነህም ወይንም የሌሎች ሳይሆን በአንድ ወጥነት የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊያን ነው።ይህን ወደዱም ጠሉም ሊለውጡት የሚችሉት ጉዳይ አይደለም።

ኢንጅነር

አሁንም አልረፈደምና እባክዎን ሕሊናዎን ይጠይቁት። የኔ የመከራ ቀን አባሪ ተባባሪዎቼ ሻለቃ ዮሴፍና ዶ/ር ታዬ ናቸው ወይስ በእወቅነት ለእውነት የቆሙትና አብረውኝ በወህኒ የነበሩት፣ ለአንዲት

ሴኮንድ እንኳን የክህደት ስሜት ያላሳዩኝ የትግል አጋሮቼ? ብለው ይጠይቁት::ለቂም በቀል ቦታ አይስጡ ለዚያውም የአስተሳሰብ ልዩነት እንጂ ሌላ ችግር የለምና ቂም በቀልም ቦታ የለውም::ቦታ ሊሰጥ የሚገባው ሃገር ሕዝብ ነው::ወጣቱ ተተኪ ትውልድ የተሻለ ሕይወት ሃገሪቱ ለእድገት ሕዝቡ ለብልጽግና የሚታደግበትን መንገድ አብረን እንቀይስ ሌላው ትርፍና አላስፈላጊ ነው ብለው ይንቁ::

ዶ/ር ታዬ እኮ በግልጽና በፊት ለፊት የቅንጅት አቋምና አመራሩን አባላቱን ጭምር እያበሻቀጡ ምን ያህል ለቅንጅት አካሄድ ንቀት እንዳላቸውና በአመራሩም ውስጥ ያሉት ስለፖለቲካ አንዳቸውም እውቀት የሌላቸው መሆናቸውን፣ሕዝቡን ገደል እየከተቱት ነው በማለት ያጣጣሉ ሰው ናቸው::

ዶ/ር ታዬ እኮ « እኔ ቅንጅትን አልመረጥኩም በማለት ያንን እንደጀብድ በየስብሰባው ላይ ሲያላዝኑ የነበሩ ናቸው

ዶ/ር ታዬ እኮ የመምሕራን ማሕበር ሕግና ደንብ ከሚፈቅደው ውጪ በፖለቲካ ድርጅት ውስጥ ዘለው የገቡና የሚያተራምሱ ሃገራዊና ሕዝባዊ አመለካከታቸው ግራ የተጋባባቸው ሰው ናቸው::

ዶ/ር ታዬ እኮ ቀደም ሲሉ ይመሩት የነበረውን ድርጅት በሕጋዊ መንገድ ያላስረከቡና ማሕበሩን ሜዳ ላይ በትነው ሃላፊነታቸውን ያልተወጡ የቀድሞው ታዬነታቸው በወቅታዊ ሰፊ ጥቅም የተለወጠ ባሕሪያቸው ያሸነፋቸው ናቸው

ደ/ር ታዬ እኮ ሕክምና ያውም ያመለካከት፣የሀገር፣ የወገን ፍቅር የከዳቸው ሕክምና የሚያስፈልጋቸው አሰተሳሰባቸው ግራ የተጋባባቸው የሚያሳዝኑ ፍጡር ናቸው

ብዙ ጊዜ ስለንጽህና በየስብሰባው ላይ ሲናገሩ ሰምቼዎታለሁ::ስለሚያነሱት ንጽህና የእርስዎን ንጽህና ቅንጣት ታህል አልጠራጠርም ያም በገንዘብ ብክነት በኩል ያለዎትን የጠራ ንጽህና አልክድም::አዎን ንጹህ ነዎት:: በሌላ በኩል ግን አንዳንድ ይጠቅሙኛል: ለኔ ይወግናሉ የሚሏቸውን ሰዎች አለአግባብ ገንዘብ እንዲከፈላቸው ብድር እንዲሰጣቸው:ለችግራቸው ማሚያ በቀን አበል ስም ክፍያ እንዲያገኙ እንደሚያደርጉ እያወቅን ግድ የለም ድርጅቱም ሲቸገር ከግል ገንዘባቸው ስለሚደጉሙ ግድ የለም እያልን በይሉኝታ አልፈነዋል::ያስታውሳሉ አንድ ጊዜ ለአንድ ሰው ቤትዎን ኮላተራል ሲያስይዙ አማክረውኝ « ይተዉ አጉል ቅያሜና ሃዘን ያስከትልብዎታል» ብልዎት አለማድረጉም ችግር አለበት ሲሉኝ አዝኜልዎት ነበር::ምክንያቱም ችግር ያሉት ጉዳይ በድርጅቱ ስብሰባ ወቅት ድጋፍ ማጣትን ነበር ሲያስቡ የነበረው ብዬ ስለምገምት ነው::

ኢንጅነር

እርስዎ ራስዎ የሚያምኗቸው የኔ የሚሏቸውና በጥርጠሬ አይን የሚያዩዋቸው አባላት እንዳሉ ደጋግመው አጫውተውኛል::ብቻ በጣም ይገርመኝ የነበረውና አሁንም ድረስ መልስ ያላገኘሁለት ጉዳይ እንዴት በአስተሳሰብና በአመለካከት ከሆዳቸው ውጪ ማሰብ ከማይችሉ ጋር እንደወገኑ ነው::ያስታውሱ ቃሊቲም እያለን አብረንዎት እንድንሠራ የታሰርን አባላት በቀይ ሽብር ተፋራጆች ግቢ እያለን የወሰኑትን የአሰራር ሂደት በመጣስና ቸል በማለት ከተወሰኑ ሁለት ሰዎች ጋር ብቻ ያውም የላእላይ ምክር ቤት ወይም የሥራ አስፈጻሚ ካልሆኑ ግን የእርስዎን እጅ አይተው ከሚያድሩ ጋር በመወገን ከሌሎቹ የሚሰነዘር ሃሳብን ችላ ማለትዎ እስከምንግዜውም የሚገርመኝ ጉዳይ ነው::ሰው እኮ ተንኮልም ሲያስብ የተሸለ ተንኮለኛና የማያጋልጥ ሁኔታም መርጦ ነው::የእርስዎ ግን መላው የጠፋ ነበር::ያስታውሱ እስቲ ከነማን ጋር ነው ስለሃገር ስለወገን ስለታሰርነው ይወያዩ የነበረው::

በማንኛውም ዞን ካሉት የሥራ አስፈጻማ አባላት  ከእርስዎ ጋር የነበራችሁት ብዙ ነበራችሁ አልነበሩም? እንቁጠራቸው፣

እርስዎ ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል፣ኢንጅነር ግዛቸው ሽፈራው፣ ዶ/ኃይሉ አርአያ፣ ዶ/ር በፈቃዱ ደግፌ፣ ዶ/ር ያእቆብ ወ/ማርያም.... ታዲያ ይህን ሃይል ይዘው ከመወሰን ከመነጋገር ይልቅ ከሌሎች ጋር ለምን መወገን መረጡ:: እውነቱን ልንገርዎ በድጋሚ፣ቀደም ሲልም አንስቼብዎት «አንተ ብዙ

ያልተረዳሃው ነገር አለ፣ እኔ እኮ እያንዳንዱ ዞን ምን እንደተሰራ እያለ ይደርሰኛል» ነበር ያሉኝ።ይህን ሲሉኝ «ሰላይ አስቀመጡብን እንዴ» ብዬ እንደቀልድ ተናግሬ ባልፈውም ያስቀመጡት ሰላይ ለቅንጅት ሳይሆን በቅንጅት ላይ ቆሞ ሆዱን ለመሙላት የመረጠ እንደሆነ ገምቼ ነበር ልክ ሆነ።

በዚያው እለት አንድ ያነሱብኝ ነጥብና አሁንም በቃለ መጠይቅዎ ላይ እንደትልቅ ወንጀል አድርገው የጠቀሱት ጉዳይ ነው።ቀደም ሲል ሲያነሱት ያሉኝ « እናንተ እኮ አይገባችሁም እነዚህ አሁን ስም ያገኙትና ወጣ ወጣ ያሉት እኮ ትላንት የተፈጠሩና በኛ በኖረ ስም ላይ የተንጠላጠሉ ናቸው» ሲሉኝ ያስታውሱ ምን አልኩዎት? ረስተውት ነውና አሁንም በቃለ መጠይቅዎ ውስጥ ያነሱት እኔ ላስታውስዎ«ኢንጅነር እኛማ ለዓመታት አዎን ነበርን እንዲሁ ስም ይዘን በምርጫም ወቅት ቢሆን እርስ በርስ እየተወዳደርን ለኢህአዴግ መመረጫ ማዳመርያ ከመሆን አላለፍንም ነበር።ስንት ዓመት ኖረን ያስገኘ ነው የፖለቲካ ለውጥ አልታየም።አሁን እነዚህ አራት ወራቸው ነው የምንላቸው ፓርቲ መስርተው ለምርጫ ባይቀርቡም ልምዱም እውቀቱም ያላቸው ናቸውና እኛ ላለፉት 17 ዓመታት ያላመጣነውን ሕዝባዊ ለውጥ አመጡ በዚህ ልንንቃቸው አይገባም በልጠው ተገኝተዋል» ብዬዎት ነበር ያን ለት እርግጥ ረግተው ቢያዳምጡኝና ያልኩትንም ሕሊናዎ እውነቱን ቢቀበልም የሰጡኝ መልስ ገን ሳቅ ብቻ ነበር፣ያልገባኝ ሳቅ። በኋላ ግን እኔም ወደቤቴ ስሄድ ሳቅሁ በእርስዎ አስተሳሰብ ሳቅሁ።

ለማንኛውም በእስር ላይ ነበረው የላእላይ ምክር ቤት ብለው እርስዎ ራስዎ የሰበሰቡትንና ውሳኔውን ሁሉ እያጸደቁ ያመኑበትን አሁን በነሻለቃና በነዶ/ር ታዬ ውትወታ ሊክዱት አይገባም።ይህን አካል መካድ ማለት ቅንጅትን መካድ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ መካድ ነውና ይቅርብዎት።

ኢንጅነር

እርስዎ በመደበኛውና በሕጋዊው ቢያንስ ቅንጅት ሕጋዊ ነው ብሎ በሚያምንበት ስብሰባ ላይ ሳይገኙ በቤትዎ ግን ያሰባስቡንና ያለምንም ችግር ያወያዩን ነበር።የዚያን እሩብ ጊዜ ለመደበኛው ስብሰባ ቢያውሉት ኖሮ አሁን የተፈጠረው ችግር አይፈጠርም ነበር።የችግሩ መንስኤ እኮ እርስዎ ነዎት።የተወሰንነውን ከድብቁ የቤት ስብሰባ ቢያገሉንም አንዳንድ ለማዳመጥ ብለው መጨረሻውን እንስማ ብለው አፋቸውን ዘግተው ይሰበሰቡ የነበሩ የሆነውን ይነግሩናል።ሻለቃ ጌታቸው ተነስቶ «እርስዎ የማይሄዱ ከሆነ እኛም የዚህ ተልእኮ አካል ልንሆን አይገባም ብሎዎት አልነበረም? ታዲያ መቼ ቀረ ደቡብ አፍሪካ ሄዶ ተመለሰ እኮ!

አሁን እርስዎ የያዙት መንገድ ተከብረን እንዳንሞት ለውርደት የሚዳርገን የጥፋት ጎዳና ነው።አሁን የያዙት ፊሊጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይቆምልኛል ያወጣኛል ብሎ እምነት የጣለበትን ፓርቲውን ማዋረድ፣የጠላት መሳለቂያ ማድረግ፣ከቅንጅት ይልቅ ራስን አስበልጦ ከሕዝብ ይልቅ ራስን አስቀድሞ ማየት ነውና መሳቂያ አይሁኑ።

ክህደትም መጠን አለው።አሁን ባሉበት ቦታ በስብሰባ ወቅት የሆነውን ስለማያውቁ ላታላቸው ብለው ከሆነ በየስብሰባው ላይ የተያዘው ቃለ ጉባኤ የስብሰባዎችን ሂደት የሚያሳይና በተገኙት አባላት የጸደቀ መሆኑን የሚመሰክር በመሆኑ ያንን ሲያዩት አለያም አስፈላጊ ሲሆን ያ ግልጽ ሲወጣ እውነቱ ይለያል።

እግዚአብሔር ለኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊያን መልካሙን ያድርግ!
እርስዎንም ከከበቡዎት የጥፋት መልእክተኞች መዳፍ ያውጣዎት!